መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ..ም

# <u>ሁለት እርምጃ ወደፊት ለመሄድ፣ አንድ እርምጃ መለስ ብሎ ታሪክን ቃኝት ማድረግ!!</u>

ክፍል 2 (ከአያልነሽ)

**እንባ እንባ ይለኛል - ይተናነቀኛል፣**
**ግን እንባ ከየት አባቱ! - ደርቋል ከረጢቱ፣**
**ሳቅ ሳቅም ይለኛል - ስቆ ላይስቅ ጥርሴ፣**
**ስቃ እያለቀሰች - መከረኛ ነብሴ።**
**(በዓሉ ግርማ)**

የተከበራችሁ አንባቢዎች!

ባለፈው የመጀመሪያ ክፍል ፅሁፌ ላይ እንደምታስታውሱት ሁለተኛውን ክፍል ተከተይ ፅሁፍ ይዥ እንደምመለስ ቃል ገብቼ ነበር፣ ቃሌን ለመጠበቅ ስል፣ እነሆ! ዛሬ ክፍል ሁለትን ትከታተሉ ዘንድ ስጋብዝ ከታላቅ አክብሮት ጋር ነው። የክፍል አንድ ፅሁፌን ያቋረጥኩት እንዲህ ብዬ ነበር ፥ . . ."<u>ለመሆኑ ስዬ አብርሃን የከረንት አፌርስ የ90 ደቂቃ ቆይታው ጠቅሞታል ወይስ ጎድቶታል?"</u> እስቲ አብረን እንዬው!!

የዛሬውን የመጨረሻ ክፍል ጹሁፌን ለእናንተ ለአንባቢዎች ግንዛቤ ይረዳችሁ ዘንድ በወቅቱ በቆይታው ላይ ለስዬ የቀርቡለትን ዋና ዋና ጥያቄዎች ከሞላ ጎደል ላስቀምጣቸው ሞክሬያለሁ። በነገራችን ላይ በዚህ አጋጣሚ የስዬን ቆይታ ሲያስተናግዱ የነበሩት 2ቱ የክፍሉ አስተናባሪዎች፣ ስዬን ሲጠይቁት የነበረው ጥያቄ የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ስሜት ያንፀባረቀና ሊጠየቅ የሚገባውን ጥያቄ ስለነበር የቀረቡለት፣ በግሌ የዕለቱን አስተናባሪዎች ሳላመሠግን አላልፍም፣ መጠየቅ የነበረበትን ጥያቄም ከሞላ ጎደል ለማንሳት ተሞክሯል ድንቅ ሥራ።

ደግ! እኔ ጥያቄዎችን (ቁም ነገሮቻቸውን) ሳይለቁ ፅሁፌን የሚያራዝሙ የመሰሉኝንና አንዳንዴም ተውጠው ለመስማት ያሰቸገሩኝን በጣም ትንሽ ቃላት ከማውጣቴ በስተቀር ዋና ይዘታቸውን ሳይለቁ እንዳለ ለማስቀመት ሞክሬያለሁ፣ በተጨማሪም ጽሁፉ እንዳይሰለች ከመስጋትም ሁሉንም የ90 ደቂቃ ቆይታ አልቀረብኩም፤ ለምሳሌ ጥያቄዎችን ብቻ እንጂ የስዬን መልስ አላካተትኩም። እንዲሁም እኔ ለዚህ ጽሁፍ ለመነሻ የመረጥኩት ጥያቄ በክፍሉ ውስጥ ከታዲሚዎቹ አንዷ የሆነችው እመቤት የጠየቀቸውን መሠረታዊ ጥያቄ አስቀድሜለሁ፤ ሴት በመሆኔም ለሴቷ እህቴ ቅድሚያውን ብሰጥ አዳልቼ ነውና "ክርስቶስ ለሥጋው አደላ" ብባላም በፀጋ ተቀባይ ነኝ።

የእህቴ ጥይቄ ይሄን ይመስላል።

ጥያቄ፥

*ስዬ ቅድም ስትናገር የሰማሁት ነገር አለ፣ ሁሉንም ትቼ ልጆቼን ማሳደግ እችል ነበር ብለኃል፣ ትችላለህ። ነገር ግን አንተ ባደረግኸው ግድያ በአርባጉጉ አካባቢ ስንት ወጣቶች ከገደል አስወርውረህ አስገደለሃል። በአሁኑ ጊዜ እነዚያ እናቶች ልጆቻቼውን ተንጥቀዋል፤ እንደ አንተም ልጆቻቸውን ለማሳደግ አልታደሉም። እኔ አንተን ለመታገል የተዘጋጀሁ ሰው ነኝ፣ የምታገልህም በብዙ መንገዶች ነው፣ አንተን በህግ ፊት ማቆምም እፈልጋለሁ፣ ስለዚህ አንተ በአሁኑ ሰዓት እዚህ መጥተህ ስለ "መድረክ" ሆነ ኢትዮጵያን ወክያለሁ ብለህ በምትከራከርበት ጊዜ ያመኛል፤ ምክንያቱም አንተም አንዱ በወንጀል የምትጠየቅ ነህና እስቲ ይሄንን መልስልኝ? እንዴትስ ሌሊቱን ተኝተህ ታድራለህ፣ ትተኛለህ? ሁለተኛ ነገር አንተ ልጆቼን አሳድጋለሁ በምትልበት ጊዜ እነዚያ ልጆቻቸውን ያጡ እናቶችና አባቶችስ ስሜታቸውን ይሰማህ ይሆን እስቲ ንገረኝ? የሚል ነው።*

እህቴ ጥያቄዋን ስታቀርብ በሲቃ ተውጣ ነበረች። በዚህ የሲቃ ስሜት ውስጥ ለምን ገባች ብሎ ለመጠየቅ ራሱ ከባድ ነው፤ እህቴ በስሜት እንድትዋጥ የሆነችበት ከበቂ በላይ ምክንያት አላትና የስሜቷንና የቁጭቷን ምንጭ እኔም ስለምጋራው ሲቃዋን በዚህ መንገድ ማስቀመጡን መርጫለሁ፥ "ነገሮች ሲመጡ እንጂ ሲሄዱ ወይም ሲያልፉ እጅግ ቀላል ናቸው" ይባላልና። በወያኔ አገዛዝ ስር የወደቀችው ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ ለማንም አሳሳቢም አስጨናቂም ነው - ታዲያ ለዚህ የማይጨነቅ ኢትዮጵያዊ እንዴት ዓይነት ሰው ነው?

ጥያቄ፥ በሌላ ግለሰብ የቀረበው ደግሞ ተከታዩ ነበር፤ እንዲህ ይላል፥

*የኢትዮ/ኤርትራ ጦርነትን በተመለከተ መነሻው ምን ነበር? አንዳንድ ግለሰቦች እንደሚያወሩት ከሆነ ጫካ በነበረባችሁበት ወቅት የተደረገ ወይም ያደረጋችሁት ሥምምነት እንደነበረ የሚገልጡ አሉ፣ በወቅቱ ደግሞ ጦርነቱን ይመሩ የነበሩት እርስዎ እንደመሆንዎ መጠን በጦርነቱ ከ70.000 በላይ ኢትዮጲያኖች አልቀዋል፤ እንደመሪነትዎ አሁን መለስ ብለው ሲያዩት ከዚያ ከጦርነቱ በኋላ ያ ሁሉ መሰዋዕትነት ተከፍሎበት የተገኘን ድል እንደገና አሳልፎ ተሰጥቶ አሁንም በተለይ (በአቶ መለስ) የአልጀርስ ስምምነት በሚል ተንጠልጥሎ የኤርትራ ጉዳይ ዛሬም አልተቋጨም፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ እርስዎ የኤርትራና ኢትዮ ጉዳይን እንዴት ይቋጫል ይላሉ?*

ጥያቄ፥

*ሌላው የክፍሉ ታዳሚ ወንድም የጠየቀው ደግሞ እንዲህ ነው፥ አቶ ስዬ እኔ የምጠይቀው ባለፉት ነገሮች ላይ ነው፣ ባለፈው ነገር ካልተሰማማን ደግሞ አሁን አብረን እንዴት እንሄዳለን በሚለው አንፃር ተመሥርቼ ማለት ነው። ከ1982 ዓ.ም - 1984 ዓ.ም ድረስ ወደ 800 ሰዎች አሠራችኋል፣ ከእነዚያም ውስጥ አንዱም እኔ ነኝ። 2 ዓመት ከ 4ወር ታሥሬአለሁ ማለት ነው፣ እና እኛው እስረኞቹ በቆፈርነው (ቦታውን ለመጥቀስ ካስፈለገ) ከሰቆጣ ደብረ ወርቅ ኮረም አራዶምና . . . የተገደሉ ጓደኞቼ አሉ 14 ናቸው ስማቸውም፥ አለማየሁ ወ/መርያም(ቤንች)፣ ዘላለም ብርሃኑ፣ ዳንኤል ታዬ፣ ደበላ ዋቆ፣ ሆሳህና ተመሠገን፣ ብንያም ሐጐስ፣ ደጋፌ በላይ፣ አህመድ፤ አስናቀ የሚባሉ ናቸው። እና አቶ ስዬ እነኝህ ሰዎች ከለ ፍርድ ቤትና ከለምንም ነገር የገደላችኋቸው ማለት ነው። ደማቸው እንዲሁ ባክኖ ቀርቶ እንዴት ነው አሁን እኔ እርስዎን አመኜ ልሄድ የምችለው?*

*በ2ኛ ደረጃ አሁን እርስዎ አሁን ወንድምዎ እንዲፈታ ይፈልጋሉ 8 ዓመት ስለታሠረ ማለት ነው፤ በርስዎ ጦር አዛዥነት የታሠሩት እነ ፀጋዬ ደብተራውስ የት ነው ያሉት? ስለነኝህ ድምፅዎን አስምተው ያውቃሉን? እና ባለፈው ነገር ላይ ይሄን ይቅርታ፣ ይሄ ነገር ደግሞ ስህተት ነው ብለው ካልነገሩን እንዴት ነው አብረን መሄድ የምንችለው። ስንቱ ኢትዮጲያዊ ነው እኮ ደሙ ፈሦ የቀረው? በትግራይ እስር ቤቶችስ ስንቱ ነው ተንገላቶ የቀረው? በማስረጃም ማቅረብ ይቻላል። እነማን እንደፈረዱባቸውም ወደ ሌላ ዞር ማለት ኢያስፈልግም፣ እነኝህን ማን እንደገደለ ለማውቅ አሁን ካስፈለገ፣ የኢ.ህ.ዴ.ን ኦዲተርና ቁጥጥር ኮሚሽን የነበሩትን አቶ ብሩክ ቢራራን መጠየቅ ይችላሉ ማለት ነው እዚያው አዲስ አበባ ስላሉ - ብዙ ሰው መጥቀስ ይቻላል። እና ይሄን ነገር እንዲመልሱልኝ ነው አመሠግናለሁ። የሚቀጥለው ጥያቄስ እንዴት ቀረበ?*

ጥያቄ፥

*አሁንም ከክፍሉ የወቅቱ አስተናጋጅ የቀረበ ጥያቄ ነው "መድረክን" በተመለከተ፥*
*አሁን በ21 ክ/ዘመን ዓለማችን ወደ አንድነት እየመጡ በአሉበትና በጋራ በሚሰሩበት ወቅት፣ እኛ አሁንም ዛሬ እንደገና ተመልሰን ወደ ጎሳ ፖለቲካ መግባቱ ፍራቻና በዜጎች መካከልም*

*መተማመን እንዳይኖር ወይም በኢትዮጵያዊነት ጉዳይ ላይ የሚንቀሳቀሱ ወገኖች ኢትዮጵያዊነት ስሜት ያላቸውን ወገኖች እንዳይሳተፉበት ያደረጋል የሚል ስጋት ያሳደረባቸው ወገኖች ስላሉ ነውና ከዚህ አንፃር "መድረክን" እንዴት ገምግመውታል?*

*- ሌላው መድረክ ለምክክር በሚባለው ስብስብ ውስጥ እርስዎና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የፖለቲካ ደርጅትን ወክላችሁ ሳይሆን በታዋቂ ግለሰብነት ስም ነው በውስጡ እንዳላችሁ የሚታወቀው፤ እንደሚያውቁት ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ታዋቂ ሰዎች አሉና እንዴት እርስዎና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ይሄንን ዕድል አገኛችሁ በተለየ ለማለት ነው?*

*- አቶ ስዬ ቅድም ሲናገሩ "መድረክ" መነጋገሪያ ነው፣ ምንም ፕሮግራም የለውም ብለዋል። እንግዲህ በትግል መስኩና በትግል ሜዳው "መድረክ" መቀጠል ካለበት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህግ መሠረት በግለሰብ ደረጃ ወደ ትግል መግባት አይፈቀደም ወይም አይቻልም፤ ምናልባት ይሄ መድረክ ወደፊት በህብረት ወይ በግንባር ወይ በቅንጅት አማክኝነት የሚዋኃድና የሚቀጥል ቢሆን እንዴት ነው ተሳትፎው ሊሆን የሚችለው? አዲስ ፓርቲ ይመሠርታሉ ወይስ አሁን እዚያው ካሉት ፓርዎች ጋር ለመቀጠል ያስባሉ? የሚቀጥሉስ ከሆነ ከየትኛው ፓርቲ ጋር? መመለስ የሚችሉ ከሆነ ።*

ሌላ ጥያቄ፥

*እስቲ መለስ ብለን እንይ። አቶ ስዬ እርስዎ የዚህ የመድረክ አባል ነዎት። እርስዎና ጥቂት የማይባሉ የዚህ የመድረክ ስብስቦች ወያኔ ሥልጣን በያዘበት ወቅት በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ነበራችሁና አገራችን አሁን አለችበት ሁኔታ ላይ እንድትወድቅ ከፍተኛ ሚና የተጫወታችሁ ናችሁ። በዚህም ብዙዎች ተጠያቂዎች ናቸው የሚሉ አሉ። ለምሳሌ በ ወደብ ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያ ያለ ወደብ እንድትቀር፣ በኤርትራ ጉዳይ ላይ ህዝብ በትክክለኛ መልኩ ሬፈረንደም እንዳያደረግ የተጫውታችሁት ሚና ፣ የሀገሪቷ መከላከያ ሠራዊት እንዲፈርስ ተደርጎ ዛሬ በአቶ መለስ ቀጥተኛ ትዕዛዝ የሚታዘዝ የራሱ የሆነ ሠራዊት እንዲፈጠር ተደርጓል . . . ወዘተ ወዘተ. እና ለዚህም ስትከሰሱ ይቅርታ አልጠየቃችሁም ይባላል፣ ለዚህ እንዲያው እርስዎ ምን ይመልሳሉ? . . .*

በወቅቱ በርካታ ጥያቄዎች የተጠየቁና የተነሱ ሲሆን እኔ እዚህ ያሠፈርኩት ከሞላ ጎደል መሠረታዊና ዋና ዋናዎቹን በአጭሩ ለማሳየት ያህል ነው።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ!

በአጠቃላይ ስዬ አብርሃ በክፍሉ ውስጥ በቆየበት ወቅት የቀረቡለት ጥያቄዎች በሙሉ ሊጠየቁ/መጠየቅ የሚገባውቸው ጥያቄዎች የነበሩ ይሁን እንጅ ስዬ ግን አንዱንም በቅጡ ያልመለሰ ሲሆን፣ ይልቁንም ቀጥተኛ መልሶችን ከመመለስ ይልቅ "አሁን ወቅቱ አይደለም" ወይንም ዛሬ የመጣሁት ስለዚህ ጉዳይ ለመነጋገር አይደለም በማለት ጥያቄዎችን አድበስብሶ ሊያልፋቸው ሞክሯል። በተቃራኒው ደግሞ የእድምተኛው ስሜትና በስክሪኑ ላይ ብቻ እንኳ በጽሁፍ ይተላለፉ የነበሩ መልዕክቶች ኢትዮጵያዊነትን ያጎሉና ከፍ ያደረጉ ነበር ማለት ይቻላል። እያንዳንዱ ግለሰብ/ሰው በውስጡ ይሰማው የነበረውን የግፍ ደወል፣ በኢትዮጵያዊነት ስሜትና ቁጣ ነበር ስዬንና የስዬን የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደረሡትን ግፍና በደል አጥብቆ የኮነነ ነበር፤ ጎሽ ኢትዮጵያዊነት እንዲህ ነው !! ። ስለ እነ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አገዳደልም ጭምር ነበር ለስዬ በስክሪኑ ላይ እድምተኛው እየፃፈ ማን ገደላቸው? እስቲ ንገረን ማን ገዳላቸው? ስዬ እባክህ መልሱን ንገረን በማለት እድምተኛው ስሜቱን ይገልጽ የነበረው። እንደ እኔ ከሆነ የ90 ደቂቃ ቆይታው ስዬን ከጠቀመው ይልቅ እንዲያውም የኢትዮጵያውያንን የጋለ ቁጣና አመቀው ይዘውት የኖሩትን የውስጥ ቁስላቸውን አውጥተው የዘረገፉበትና የነገሩበት ነው። እንዲያም ሆኖ ግን በርካታ እጆችም ለጥያቄ ወጥተው የነበር ቢሆንም፣ የሰው የቁጣ ስሜትና የወጣው እጅም ሁሉ እደተንተለጠለ በጊዜ እጥረት ይሁን

በሌላ ምክንያት ውይይቱ ሊቋረጥ በቅቷል። ለማንኛውም በጥቅሉ 90 ደቂቃው ለስዬ የተመቼ ነበር ለማለት አያስደፍርም።

በአጭሩ በቆይታው የተላለፈለው ቁም ነገር፣ ለእነ ስዬና መሠሎቻቸው (ልብ ካላቸው) የእድምተኞቹ የመልእክት ይዘት በሙሉ፣ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በአጠቃላይ ያደረሳችሁት ግፍና በደል ተቆጥሮና ተዝቆ አያልቅምና አሁን ያገኛችሁትን አጋጣሚ ተጠቅማችሁ ወደ ህሊናችሁ በመመለስ የበደላችሁትንና ያሳዘናችሁትን ሕዝብ ይቅርታ ጠይቁ የሚል ነው። በተጨማሪም ይህ ዕድል አሁንም በእጃችሁ ውስጥ ስለገባና ስለአለ ለይቅርታ ተጠቀሙበት የሚል ነው በአጭሩ።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ !

አሁንም እደግመዋለሁ። ይቅርታን በተመለከተ ይቅርታ ጠይቁ ማለት ለፍርድ ቅረቡ ማለት አይደለም። አንድ ሰው ይቅርታን እንዲጠይቅ (ሲሆን በፈቃዱ) የሚገደደው፣ ያጠፉ ሲመስለው ወይም ከመሰለው ይቅርታ መጠየቁ መሠልጠንን ያመላክታል እንጂ ይቅርታ መጠየቅን በራሱ እንደ ነውር ቆጥሮ እንደ ነፍሰ ገዳይ የምንሸሽበት፣ ይልቁንም በሕግ አግባብ ከሚከናወን ፍትህና ህግ ጋር ማያያዝ ፈጽሞ፣ ፈጽሞ ትልቅ ስህተት ነው። ምን ማለት ነው! አንድ ሰው አውቆም ሆነ ሳያውቅ ቢሳሳት ይቅርታ ለመጠየቅ የሚያስችለውንና የሚያበቃውን ቅንነት፣ ወደሌላ ጽንፍ ለጥጦና ውሰዶ በሌላ መንገድ መተርጎም የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን የሞራል እሴት ይበልጥ የሚሸርሽር ነው። ይቅርታን መጠየቅ በመሠረቱ ከፍትህ አግባብና ሂደት ጋር ማያያዝ ትክክል አይደለም። ይቅርታ ማለትና ፍትህ በፍጹም አይገናኙም። እርግጥ ነው የሚሠራ ይሳሳታል - ነገር ግን ስህተትን በጊዜ ተርድቶ ደግሞ በ (በሽፍጥ) ሳይሆን በቅንነት ይቅርታ መባባልን እያንዳንዱ ሰው የሕይወቱና የህይወታችን መመሪያ ልናደረገው ይገባል ባይ ነኝ፣ ካልነበረም ይጀመር፣ ከነበረም ይጠናከረ፣ ሲጠናከረ ደግሞ የዕለት ዕለት መሣሪያችን ይሁን/እናድርገው ባይ ነኝ። ወገኖቼ! ምንም የሚያስወጣን ወጭ የለም። ይኸው ነው እውነታው።

- <u>ይቅርታ የሚባለው ቃል</u> ከሁሉም ነገር በላይ የከበረና ውድ ነው። ይቅርታ የሚለው ቃል ለትንሽ ሆነ ለገዘፈ ስህተት መመለሻና ማለስለሻ ቅቤ ነው። ይቅርታ የማለት ተፈላጊነቱ፣ በዓለም ላይ ላሉ ፍጥረታት በሙሉ የሰው ልጆች ሆኑ አዕዋፍ፣ እንስሳትም ሁሉ ለሚፈልጓትና ለሚመኟት፣ የሰው ልጅ ሁሉ ለሚዘምሩላትና ለሚናፍቋት፣ በየደጀ ሠላሙ ለሚፀልዩላት ሠላም ጋ ለመድረስ፣ የመድረሻዋ ድልድይ ይቅርታ የምትለዋ ቃል በመሆኑ ነው።
- <u>በይቅርታ ፈታውራሪነት፥</u> የተገነባችና የምትቆም **ሠላምን** የሚንቀንቃት ምድራዊ ኃይል የለም። በተጨማሪም ይቅርታ በማንኛችንም በኩል ቢሆን የምታሠክፍለው ምንም የሰው ሕይወት የለም።
- <u>ይቅርታ የምትለዋ ቃል</u> ፥ ግፋ ቢል የምትጠይቀው፣ ከባዱና አስቸጋሪው መዘዟ፣ ከሸፍጥ የነፃ ቅንነትን፣ ከቂም የነፃ ደግነትን፣ ከአውሬነት ይልቅ የተሻለ ሰውነትን የምትጠይቅና የምታገዝፍ፣ እንዲሁም ከልብ የሚፈልቀውን ይቅርታ ባይነትን በአፍ እንዲወጣ ለማደርግ ማስጨንቋ ነው።
- <u>ይቅርታ የምትለዋ ቃል፥</u> ሕሊናን ሁሌ ለሚያስጨንቁ ክፉ ድርጊቶች ሆኑ ግፎች ለማጠቢያና ለመጠገኛ የምታገለግል፣ ነገር ግን በእያንዳንዳችን ሰብእና ላይ ክፋትን በሚያስብ ልቡና ውስጥ ከተቀበረችበት አውጥቶ ነፍስ መዝራት።
- <u>ይቅርታ የሚባለው ቃል፥</u> በየዕለት ህይወታችንም ሆነ ማህበራዊ ግንኙነታችን ጭምር አብሮን መኖር መጓዝ ያለበትና ሊኖርም የሚገባው ድንቅ አሴት ነው፣ ስለሆነም ከሌለ እንዲኖር ማደረግ፣ ካለም እንዲያብብ መከትኮት፣ ለዘላለም በህይወታችን አሴት አድርገነው እንዲቀጥል ደግሞ እያንዳንዳችን ውሃ ማጠጣት፣ ማቀፍ፣ መደገፍና

ማበረታታት ይኖርብናል። በአጠቃላይ የህይወታችን ቀዳሚ መመሪያ፣ ለተሳሳትነውና ላጠፋነው ነገር ሁሉ መነሻችንም ፣ ይቅርታ የሚለው ቃል መሪ ቀንዲላችን ልናደርገው ይገባል ባይ ነኝ።

አቶ ስዬ ሆይ! የወያኔ የፖለቲካ አካሄድ ከጅምሩ ጀምሮ እጅግ የተበላሸና "ከደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ" እንዲሉ በዚሁ ላይ ደግሞ እጅግ ጠቦ፣ በመንደርና በጎጥ የተኮለኮለ ስለነበረ በዘረኝነት፣ በሽረና በተንኮል ከመተብተብ አያመልጥም ነበር። በሀገር ደረጃ በሥልጣን ኮርቻም ተጀቡኖ በሕገ መንግሥት ሽፋን፣ ሕገ-ጠባብነት አገር ላይ አስፍኖ አገርን ከማጥፋቱ በፊት፣ መርኃ-ግብራችሁ በህዝብ ብዙ ተቃውሞ የገጠመው ነበር ፤ ሥልጣን ከተወጣ በኋላም ቢሆን በኢትዮጵያችን የተደረገውና እየተደረገ ያለው አሁን በአደባባይ የሚታዬው ነው። እናም ጥያቄያችን አሁንም ቢሆን የሚያነጣጠረው፣ የይቅርታችሁ የመጀመሪያው እርምጃ ከፖለቲካው ራሳችሁን አግልላችሁ በማናቸውም ፖለቲካ ውስጥ እጃችሁን ከማስገባት ተቆጠቡ የሚል ነው። ይሄ የመጨረሻ ትንሹ ጥያቄ ነው አቶ ስዬ። እንደ እውነቱ ከሆነ - ሀብት አፍርታችኋል፣ ቤተሰብም መሥርታችኋል፤ ሲሆን ሲሆን በዚያ ኃብታችሁ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ህዝብ የሚጠቅምና የሚክስ ሠብዓዊ ተግባር ብታከናውኑ፣ አሊያ ግን ለልጆቻችሁ ለወደፊት እጣ ፈንታ የሕሊና ቁስልና ጠባሳ የሚያሽር ነገር በቀሪው ዕድሜያችሁ እየሠራችሁ እለፉ ነው የጥሪያችን አንኳር መደምደሚያ። ከእነ ሠምሃል መለስ ዜናዊ ፣ ከነ ብሌን ታምራት ላይኔ፣ ከእነ ትእግስት መንግስቱ ኃ/ማርያም የሰቀቀን ሮሮና ኑሮ ልትማሩ ይገባልና። ልጆቻችሁን ካልወደዳችሁ እኛን የሩቆቹን ለመውደዳችሁ ብንጠራጠር አትፍረዱብን። አዝናለሁ!! ልጆች ሁሉ በማይመለከታቸውና በማያውቁት፣ ባልዋሉበት ነገር ሁሉ በሕሊና ጭንቀት መስቃየታቸውና እንዲኖሩ መደረጉ እጅግ ልብ ይሠብራል። እርቅ፣ ሠላም፣ እና ፍቅር የሚቆሙት፣ ቅንነትና ንጽህና በተሞላበት በይቅርታ የድልዳል ንጣፍ ላይ ነው።

አንርሣ! ቴዲም እኮ ያሠተሰርያል ያለው፣ ከዚህ ጭንቀቱ ተነስቶ ሳይሆን ይቀራል ትላላችሁ!!
አመሠግናለሁ

የሕዝብ ድምፅ ይከበር! የታሰሩ የፖለትካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላዓለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን።
march 12/2009